ወጋገን ባንክ (አ.ማ.)
WEGAGEN BANK S.C.

የባለአክስዮኖች 32ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ
ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 32

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ

ሀ. ቀን፦ መስከረም 27 ቀን 2018 ዓ.ም

ለ. ሰዓት፦ ከጠዋቱ3:10 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 6፡10 ሰዓት ድረስ

ሐ. ቦታ፦ አዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል

2. የጉባኤው ፕሪ አደራረግ

ይህ የባለአክሲዮኖች 32ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ህግ፣ አንቀጽ 366(1)፣ አንቀጽ 367(1) እና አንቀጽ 370 መሠረት ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ ጳጉሜ 2 ቀን 2017 ዓ.ም በታተሙ አዲስ ዘመን እና ሪፖርተር ጋዜጦች፣ እያንዳንዱ ባለአክስሲዮን ባስመዘገበው ሞባይል ቁጥር SMS በመላክ፣ በባንኩ ማህበራዊ ገጾች፣ በኢቲቪ እና ፋና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች፣ በፋናና ሸገር ሬዲዮ አማካኝነት እንዲሁም በባንኩ ድረ ገጽ (www.wegagen.com) በመስጠፍ በወጋገን ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠርቷል።

3. የጉባኤው ሰብሳቢ፣ ድምጽ ቆጣሪዎች፣ ጸሐፊ፣በጉባኤው የተገኙ ዳይሬክተሮች እና ታዛቢዎች

3.1 የጉባኤው ሰብሳቢ

የንግድ ህጉ አንቀጽ 379(1) በሚያዘው መሰረት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ አብዲሹ ሁሴን የጉባኤው ሰብሳቢ በመሆን ስብሰባውን መርተዋል።

3.2 የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች እና የጉባኤው ጸሐፊ

ጉባኤውን ለመጀመር በንግድ ህጉ አንቀጽ 380(1) እና የባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 16 (3) በሚያዙት መሰረት በጉባኤው በባለአክሲዮንነት ወይም በወኪልነት ከተገኙ እና ፍቃደኛ ከሆኑት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች መካከል በተደረገ ስምምነት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ ለማቸው የተዘረዘረው ሁለት ባለአክሲዮኖች የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች ሆነው ተመርጠዋል። እንዲሁም የማህበሩ ጸሐፊ አቶ ሓዱሽ ህንፃይ የጉባኤው ጸሐፊ ሆነው ተሰይመዋል።

ተ/ቁ	ስም	ኃላፊነት	የተወካይ ስም
1	መሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ድምጽ ቆጣሪ	አቶ ክብረአብ ተወልደ
2	አቶ ሙሉጌታ መኮንን	ድምጽ ቆጣሪ	-
3	አቶ ሓዱሽ ህንፃይ	የጉባኤው ጸሀፊ	-

3.3 <u>በጉባኤው የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት</u>

ተ/ቁ	ስም	ተወካይ	ኃላፊነት
1	አቶ አብዲሹ ሁሴን	-	ሰብሳቢ
2	አቶ ወልደገብርኤል ናይዝጊ	-	ም/ሰብሳቢ
3	አቶ ፍቅሩ ጂሬኛ	-	አባል
4	አቶ ፍትሃነገስት ገብሩ	-	አባል
5	ሚጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	አቶ ገብረእግዚአብሄር ሓዱሽ	አባል
6	ሱር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር	አቶ ዘንፉ አስፋው ገ/ትንሳኤ	አባል
7	አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/ የግል ማህበር	አቶ ሀሰን የሱፍ	አባል
8	ኢዛና መአድን ልማት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር	አቶ ተስፋፅዮን ደስታ ተሰፋ	አባል
9	አቶ ሱራፌል በርሀ ወልዱ	-	አባል

3.4 <u>በጉባኤው ያልተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት</u>

1	ትእምት	አቶ አስምሰገድ አሰፋ	አባል

3.5 <u>በጉባኤው የተገኙ ታዛቢዎች</u>

ተ/ቁ	ሙሉ ስም	የወከላቸው ተቋም
1.	አቶ ማስተዋል አምባዬ	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
2.	አቶ ሳሙኤል መንግስቱ	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
3.	ወ/ ገነት ታደሰ	ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

4. ምልዓተ ጉባዔ

4.1. ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ አባላት ብዛት 15,321

4.2. ጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ የአክስዮን ብዛት 7,590,449

4.3. በጉባኤው የተገኙት የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት1,483 ሲሆኑ የያዙት የአክሲዮን ብዛትም 3,873,971 (51%) ነው። በጉባኤው ያልተገኙ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ብዛት 13,838 ሲሆኑ የያዙት የአክስዮን ብዛት 3,716,478 (49%) ነው። ጉባኤውን ለመጀመር አስፈላጊ የሆነ አነስተኛ የአክስዮን ብዛት 1,897,612 ወይም (25%) ነው።

በዚሁ መሠረት በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 16(5) እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 398(1) መሠረት ከጠቅላላ የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) 25% በላይ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ስለተገኙ በጉባኤው አጀንዳዎች ላይ ተወያይተው ውሳኔ ለማሳለፍ ስልጣን ያላችው ስለመሆኑ በድምጽ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል። በጉባዔው የተገኙትን ወይም ወኪል የላኩትን ባለአክሲዮኖች ስምና አድራሻቸው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለውን የአክሲዮን መጠንና የሚሰጠው የድምጽ ቁጥር የሚያሳይ የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ጋር አባሪ ሆኖ ተያይዞ ቀርቧል።

5. የጉባኤው አጀንዳዎች

5.1 አጀንዳዎችን ማጽደቅ፤

5.2 አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፤

5.3 የአክሲዮኖች ዝውውርን ማሳወቅ፤

5.4 እ.ኤ.አ የ2024/2025 የስራ ዘመን አፈጻጸም የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ተወያይቶ ሪፖርቱን ማጽደቅ፤

5.5 እ.ኤ.አ.የ2024/2025 የስራ ዘመን የውጭ ኦዲተሩን ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ፤

5.6 እ.ኤ.አ የ2024/25 የስራ ዘመን በተጣራ ትርፍ አደላደል ላይ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

5.7 እ.ኤ.አ የ2024/25 የስራ ዘመን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ክፍያ እና የ2025/26 የስራ ዘመን ወርሃዊ አበል ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

5.8 እ.ኤ.አ.የ2025/26 የስራ ዘመን የባንኩን ሂሳብ የሚመረምር የውጭ ኦዲተር ሹመት ማጽደቅ፣ ክፍያውን መወሰን፣ እና

5.9 በረቂቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና ምርጫ (የተሻሻለ) መመሪያ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ ናቸው።

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ማጠቃለያ፣ የተሰጡትን ድምጾችና ውሳኔዎች፣

6.1. አጀንዳ 5.1፣ አጀንዳውን ማጽደቅ

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

የጉባኤው ሰብሳቢ ለስብሰባው የተያዙ አጀንዳዎች ዝርዝር ከገለጹ በኃላ በተያዙት አጀንዳዎች ላይ የሚቀርብ አስተያየት፣ ተቃውሞ ወይም ድምፀ-ተአቅቦ ካለ ተጠይቆ ባለመቅረቡ ሰብሳቢው በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረቡትን አጀንዳዎች ጉባኤው እንዲያጸድቅ ጠይቀዋል።

ለ. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና ጉባኤው ያሳለፈው ውሳኔ

ጉባኤው በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረቡትን አጀንዳዎች በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

6.2. አጀንዳ 5.2፣ አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

እ.ኤ.አ ከኅዳምበር 1 ቀን 2024 እስከ ኦክቶበር 2 ቀን 2025 ድረስ ቁጥራቸው 154 ሚሆኑ አዲስ ባለአክሲዮኖች ብዛታቸው 84,699 የሆኑ አክሲዮኖችን ከነባር ባለአክሲዮኖች ተላውረውላቸው፤ እንዲሁም ባንኩ ለህዝብ ካወጣው አዲስ የአክሲዮን ሽያጭ ብዛታቸው 203,487 የሆኑ አክሲዮኖችን በመግዛት ቁጥራቸው 872 የሆኑ አዲስ የማህበረ ባለአክሲዮን መሆናቸውን ጉባኤው አውቆ እንዲቀበለው ሰብሳቢው ጠይቀዋል። (ሰንጠረዥ ተያይዟል)

ለ.የተሰጡት ድምጾች ውጤት እና ጉባኤው ያሳለፈው ውሳኔ

እ.ኤ.አ ከኅዳምበር 1 ቀን 2024 እስከ ኦክቶበር 2 ቀን 2025 ድረስ ከነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ተላውሮላቸው እንዲሁም አዲስ አክሲዮኖችን ከባንኩ በመግዛት የማህበረ አባል የሆኑ 1026 አዲስ ባለአክሲዮኖችን ጉባኤው አውቆ አባልነታቸውን በሙሉ ድምጽ ተቀብሏል።

6.3. አጀንዳ 5.3፣ የአክሲዮኖች ዝውውርን ማሳወቅ

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

በባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 9 መሠረት እ.ኤ.አ ከኅዳምበር 1 ቀን 2024 እስከ ኦክቶበር 2 ቀን 2025 ድረስ ቁጥራቸው 50 የሆኑ ነባር ባለአክሲዮኖች ብዛታቸው 6,409 የሚሆኑ አክሲዮኖችን ለነባር ባለአክሲዮኖች ያስተላለፉ መሆኑን ጉባኤው አውቆ እንዲቀበለው ሀሳብ ቀርቧል። (ሰንጠረዥ ተያይዟል)

ለ. የተሰጡት ድምጾች ውጤት እና ጉባኤው ያሳለፈውን ውሳኔ

እ.ኤ.አ ከኅዳር/ምበር 1 ቀን 2024 እስከ ኦክቶበር 2 ቀን 2025 ድረስ ቁጥራቸው 50 የሆኑ ነባር ባለአክሲዮኖች ብዛታቸው 6,409 የሚሆኑ አክሲዮኖችን ለነባር ባለአክሲዮኖች ያስተላለፉ መሆኑን ጉባኤው አውቆ እንዲቀበለው የቀረበውን ሀሳብ ጉባኤው በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

6.4. አጀንዳ 5.4፣ እ.ኤ.አ የ2024/2025 የስራ ዘመን አፈጻጸም የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በቅድሚያ ባለአክሲዮኖች የባንኩን 32ኛ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲሳተፉ የተደረገውን ጥሪ አክብረው በመገኘታቸው በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና በራሳቸው ስም ልባዊ ምስጋናቸውን ካቀረቡ በኃላ እ.ኤ.አ. ጁን 30 ቀን 2025 በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ባንኩ ባደረጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ውጤቶች፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችን እንዲሁም ቀጣይ አቅጣጫዎች ያካተተ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት በንባብ አስምተዋል፡፡

ሰብሳቢው ባቀረቡት አመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት በባንኩ የስራ ክንዋኔ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ የነበራቸውን አጠቃላይ አለማቀፋዊና ሀገራዊ የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ኢንዱስትሪ ሁኔታዎችን ከገለፁ በኋላ በበጀት ዓመቱ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርሞች የፈጠሯቸውን መልካም እድሎች እና ስጋቶችን በሚገባ በማጤን ባንኩን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎችን በመለየት እና ተገቢውን ዝግጅት በቅንጅት በማከናወን ውጤታማ ስራዎች ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን ሰብሳቢው አስታውቀው፤ በበጀት ዓመቱ በሀገሪቱ የካፒታል ገበያ ስራ መጀመር ጋር ተያይዞ ባንኩ በኢንዱስትሪው የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓስ ንዋዮች ገበያ በቀዳሚነት በመመዝገብ እና በካፒታል ገበያው ያለውን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እጥረት ለመሙላት የመጀመሪያውን የግል የኢንቨስትመንት ባንክ "ዘመን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ አ.ማ." በማቋቋም ፈር ቀዳጅ ለመሆን መቻሉን ሰብሳቢው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ወቅታዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ ውጤታማ አሰራሮችን በመዘርጋት የባንኩን ተወዳዳሪነት እና የገበያ ድርሻ ከማሳደግ ባሻገር በዘርፉ በሚፈጠሩ አዳዲስ እድሎች በቀዳሚነት ተጠቃሚ እንደሆነ ሰብሳቢው የተከናወኑት ፈርቀዳጅ ተግባራት ለባንኩ ቀጣይ የስኬት ጉዞ መሰረት የሚጥሉ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

በተጨማሪም ሀገራዊ እና በኢንዱስትሪ ደረጃ ያጋጠሙ የዋጋ ንረት፣ የገንዘብ እጥረት፣ የፀጥታ ስጋት እና የንግድ መቀዛቀዝ ተግዳሮቶች በባንኩ የስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረው የነበሩ ቢሆንም እነዚህን ፈተናዎች ለመቋቋም የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ በመተግበር በ2024/25 በጀት ዓመት ባንኩ በታሪኩ ከፍተኛ የሆነውን ከታክስ በፊት ብር 3.85 ቢሊዮን እንዲሁም ከታክስ በኋላ ብር 2.78 ቢሊዮን ትርፍ ማስመዝገብ መቻሉን ሰብሳቢው ገልጸዋል። ባንኩ ይህንን ውጤት ሊያስመዘግብ የቻለው ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ ለውጦችን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሁኔታዎችን በውል በመረዳት ተገቢ የሆኑ ስትራቴጂዎችን ቀርፃ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማለትም ቦርድ፣ ማኔጅመንት፣ ሰራተኞች፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ተግባራዊ በማድረጉ እንደሆነም ሰብሳቢው አስረድተዋል።

በተያያዘም በፋይናንስ ኢንዱስትሪው የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ለመቋቋም እና እድሎችን የመጠቀም አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን አዳዲስ የባንክ አገልግሎቶችን በማቅረብ እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅምን የማሳደግና ዲጅታላይዜሽንን ማስፋፋት ላይ በትኩረት ሲሰራ መቆየቱን አብራርተዋል።

ባንኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የላቀ አፈፃፀም እንዲያስመዘግብ ያስቻሉትን የተለያዩ ቁልፍ ተግባራት ሰብሳቢው የዘረዘሩ ሲሆን ከነዚህም መካከል፣

- ቦርዱ በበጀት ዓመቱ 25 ስብሰባዎችን እንዲሁም አራቱ ንዑስ ኮሚቴዎች በድምሩ 31 ስብሰባዎችን በማካሄድ የባንኩን አፈፃፀም የመገምገምና አሰራሮችን የመዘርጋት እንዲሁም የመቆጣጠር ኃላፊነታቸውን በሚገባ ሲወጣ የቆየ መሆኑን፣ በተጨማሪም ቦርዱ ከማኔጅመንቱ ጋር በቅርበት በመገናኘት በየወሩ የአቅድ አፈፃፀም እና አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ሁኔታ ግምገማ በማድረግ ለማኔጅመንቱ ግልፅ የስራ አቅጣጫ በመስጠት ባንኩ በኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅ እንዲሁም የገበያ ድርሻውን እንዲያሳድግ ያልተቆጠበ ድጋፍ ማድረጉን፣ የባንኩን አሰራር ለማቀላጠፍ እና የመልካም አስተዳደር ስርዓት /Corpoarte Governance/ እንዲሰፍን እንዲሁም ተገቢ የስጋት አስተዳደር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችን በማፅደቅ ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረጉን፣ በተመሳሳይ የቦርድ ንዑስ ኮሚቴዎችም በየዘርፋቸው ተገቢ የሆነ ክትትል ሲያደርጉ እና የቅርብ አመራር ሲሰጡ የቆዩ መሆኑን፣ በተያያዘም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት አፈፃፀም ግምገማ መመሪያ መሠረት ቦርዱ የራሱን፣ የንዑስ ኮሚቴዎችን እና አባላቱን ዳይሬክተር የነበረው አስተዋፅኦ ላይ ክትትል እና ግምገማ ማድረጉን የተገለጸ ሲሆን በግምገማው ቦርዱ ከማኔጅመንት ጋር በመቀናጀት የባንኩ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂካዊ ግቦች

ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ አመርቂ ውጤት የተገኘ መሆኑንና መሻሻል ያስባቸውን ክፍተቶች በስልጠና እና በተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለማሟላት የሚሰራ እንደሚሆን ሰብሳቢው ገልጸዋል።

- የባንኩን የተወዳዳሪነት አቅም ለማሳደግ በባንኩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ትኩረት በተሰጣቸው የሃብት ማሰባሰብ፣ የሰው ኃይል ልማት፣ የአሰራር ልህቀት፣ ካፒታል ማሳደግ፣ የገፅታ ግንባታ፣ ቀልጣፋ የደንበኞች አገልግሎት መስጠት፣ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ ጥራት ያለው የዲጅታል ባንክ አገልግሎት አቅርቦትን ማስፋፋት፣ ትርፋማነትን ማሳደግ፣ የስጋት ክትትል እና መልካም አስተዳደር ማጠናከር ተግባራት ላይ ዝርዝር እቅድ አውጥቶ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን ሰብሳቢው ጠቅሰው፤ ወጪን ለመቆጣጠር እና የባንኩን አገልግሎት ምቹ እና ቀልጣፋ በማድረግ የደንበኞችን እርካታ ለማሳደግ ያለሙ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት ውጤታማ ስራዎች መከናወናቸውን አብራርተዋል።

- በተጨማሪም ሰብሳቢው በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ወቅታዊ የባንኩን የውስጥ እና የውጪ ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ ተግባራዊ የተደረገውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ለመፈፀም የሚያስችል የመዋቅር ክለሳ መደረጉን፣ በዚህም መሰረት የዲስትሪክቶችን እና የቅርንጫፎችን አፈፃፀም የበለጠ ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የአደረጃጀት ክለሳ ተግባራዊ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸዋል።

ባንኩ በዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅ ለማስቻል የሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ሰራተኞች በሙያቸው በቂ እውቀትና ክህሎት በመጨበጥ በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን፤ በተጨማሪም ነባሩን የስራ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት በመከለስ የባንኩን ስትራቴጂክ ግቦች ይበልጥ ለማሳካት የሚረዳ እና ውጤት ተኮር የሰራተኛ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት ተግባራዊ መደረጉን፣ ከዚህም ጋር በተያያዘ በሲንዲስትሪው ያለውን የክፍያ ሁኔታ በማጥናት የሰራተኞችን ተነሳሽነት ለማሳደግ እና ለባንኩ ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም ዓመታዊ እቅድ መሳካት ያላቸውን አስተዋፅኦ ይበልጥ ለማሳደግ የደመወዝ ጭማሪ እና የነፍስ ክፍያ ተፈፃሚ መደረጉንና ይህም በሰራተኞች ዘንድ የስራ መነቃቃት መንፈስ ለመፍጠር አስችሏል አብራርተዋል።

በተጨማሪም የማኔጅመንቱን እውቀት እና ክህሎት ማዳበር የሚያስችሉ ስልጠናዎች እና የተሻለ የውጭ ልምድ የመቅሰም ሰፊ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ባንኩን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር አቅም ለመፍጠር እንዳስቻለ ሰብሳቢው ገልጸው፣ ይህም ማኔጅመንቱ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን አቅዶ የመፈፀም

አቅም እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የመስጠት እንዲሁም የባንኩን ስትራቴጂክ አላማዎች የመተግበር አቅም በላቀ ደረጃ ለማገልበት እንዳስቻለ አስረድተዋል።

ሰብሳቢው አያይዘውም አዲስ ስተከፈቱ የስራ ክፍሎች እና ቅርንጫፎች አስፈላጊውን የሰው ኃይል ለማሟላት 127 አዲስ ሰራተኞች የተቀጠሩ መሆኑንና በዚህም እ.ኤ.አ ጁን 30 ቀን 2025 ላይ የባንኩ አጠቃላይ የሰራተኞች ብዛት 5,553 መድረሱን አስታውቀዋል።

በሴላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እያገኘ በመጣው ዘለቄታዊ እድገት፣ የአካባቢ፣ የማህበራዊ እና የአስተዳደር መስፈርቶችን የተመለከተ ፖሊሲ ተቀርፃ ተግባራዊ በማድረግ ባንኩ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ የቢዝነስ አስተዳደር ስርዓት በመተግበር በሲንዲስትሪው ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸው፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ባንኩ ለህብረተሰቡ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ያለውን አጋርነት ለመግለፅ በአካባቢ ጥበቃ፣ በማህበረሰብ ድጋፍ፣ በበጎ አድራጎት እና የልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ የራሱን አሻራ እያሳረፈ እንደሚገኝ፤ ከዚህ አንፃር ባንኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በበጎ አድራጎት ስራ ለተሰማሩ ተቋማት እንዲሁም መንግስት የጀመራቸውን የተለያዩ የልማት ስራዎች ለማገዝ በአጠቃላይ የብር 29.8 ሚሊዮን የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉንና ይህም ባንኩ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን መልካም ስም የበለጠ እንደሚያሳድገው መታመኑን አስገንዝበዋል።

ሰብሳቢው አክለውም ባንኩ በሰራተኞች፣ በሥራ መሪዎች፣ እና በባለአክስዮኖች ስብጥር መላ ኢትዮጵያውያንን ያሳተፈ እንደሆነና ይህንንም ለማጠናከር እኩል ሥራ እድል በመስጠት፣ በተለይ የሴት ሥራ መሪዎችን በቁጥር እና በደረጃ ለማሳደግ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የባንኩ ባለድርሻ እንዲሆን ለማስቻል አክስዮኖቹን ለህዝብ ክፍት በማድረግ ሲሰራ የቆየ መሆኑንና ይህም ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑ አስታውቀዋል።

በሴላ በኩል ባንኩ የአገልግሎት ተደራሽነት እና አካታችነትን ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ሲያከናውን የቆየ መሆኑና ከመደበኛ የባንክ አገልግሎቶች በተጨማሪ ወጣት ስራ ፈጣሪዎችን በተለይም ሴቶችን ታሳቢ ያደረጉ የዲጂታል ብድር አገልግሎቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻሉን፤ በዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በባንክ አገልግሎት ተደራሽነት እና አካታችነት ላይ ባደረገው ጥናት በሴቶች አካታች የባንክ አገልግሎት የምዘና መስፈርት መሰረት ወጋገን ባንክ ሁለተኛ ከመውጣት ለሁሉም ህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነት ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር ያሳየ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸዋል።

የካፒታል ገበያ መጀመር ተከትሎ ባንኩ አስፈላጊ መስፈርቶችን በማሟላት በቀዳሚነት የተመዘገበ ኩባንያ በመሆን አክሲዮኖቹን በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓስ ንዋዮች ገበያ ላይ በማስመዝገብ ወደ ገበያ መውጣቱ ተጨማሪ ካፒታል ለማሰባሰብ የሚያስችለውን ዕድል ከመፍጠሩ በተጨማሪ ለባለአክሲዮኖችም ለአክሲዮኖቻቸው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለማግኘት እንዲሁም ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ አክሲዮኖቻቸውን ለመገበያየት የሚያስችላቸው እንደሚሆን ሰብሳቢው አስረድተው፤ በባንኩ ወሳኝ ባለቤትነት የተቋቋመው ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክም ባንኩ የሚሰጣቸውን የባንክ አገልግሎቶችን በማስፋት እና ለደንበኞቹ የተለዩ የኢንቨስትመንት ባንክ አገልግሎቶች በማቅረብ በኢንዱስትሪው ያለውን ተወዳዳሪነት እና የገበያ ድርሻ ያሳድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል። በሌላ በኩል ኢንተርናሽናል ፋይናንስ ኮርፖሬሽን (አይ-ኤፍ-ሲ)፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ ኮመርዝ ባንክ፣ እና ሲቲ ባንክ ከመሳሰሉ የተለያዩ አጋር ድርጅቶች እና ስመጥር ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር አጋርነት በመመስረት ልምድ መቅሰም እና የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት መቻሉን አስታውቀዋል።

ባንኩ አሁን ከሚገኝበት የዋና መ/ቤት ህንፃ በተጨማሪ በተለያዩ የክልል እና የዞን ዋና ዋና ከተሞች የራሱን ህንፃ ለመገንባት አቅዶ እየሰራ መሆኑንና በመቐለ ከተማ 3500 ካ.ሜ ቦታ ላይ G+25 ህንፃ ግንባታ ለማስጀመር በግልጽ ጨረታ የኮንትራክተር መረጣ በማድረግ በብር 1.5 ቢሊዮን የስትራክቸር ግንባታውን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማከናወን ከጨረታው አሸናፊ ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ ጋር የኮንትራት ስምምነት ውል በመፈራረም ግንባታውን ለመጀመር የቦታ ርክክብ ተፈጽሞ የህንፃ ግንባታውን በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸዋል።

በተጨማሪም ባንኩ ባለፉት በርካታ ዓመታት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፉ እና ዘመኑን የዋጁ የባንክ አገልግሎቶችን ተደራሽ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በኢትዮጵያ የባንክ አገልግሎት የልህቀት ተምሳሌት ለመሆን የሰነቀውን ራዕይ ለማሳካት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የዲጂታል ባንኪንግ አቅሙን ለማሳደግ ከፍተኛ በጀት መድቦ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ሰብሳቢው ገልጸው፤ በስትራቴጂክ አቅዱ ያስቀመጠውን የዲጅታል ልህቀት ለማረጋገጥ አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ስራዎች እየተገበረ መሆኑንና በዚህም "እፎይታ" የተሰኘ የዲጅታል ብድር አገልግሎት እንዲሁም ከኢ-ብር ጋር የአጋርነት ስምምነት በመፈራረም "ወጋገን ኢ-ብር ሞባይል ዋሌት" የተሰኘ የሞባይል ገንዘብ እና የወኪል ባንክ አገልግሎት ተግባራዊ መደረጉን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የደንበኞችን ፍላጎት ይበልጥ ለማርካት ምቹ፣ ቀልጣፋ እና ደህንነታቸው የተጠበቀ አዳዲስ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ከዘርፈ ብዙ የቻናል አማራጮች ጋር በማቅረብ ደንበኞች የላቀ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑን ሰብሳቢው ጠቅሰው፤ የትምህርት ቤቶችን የመማር ማስተማር ስራ የሚያዘምኑ፣ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት አገልግሎቶችን ክፍያ ስርዓት የሚያቀላጥፉ፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ለአባሎቻቸው የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች የሚያሻሽሉ የተለያዩ የዲጂታል ባንክ አገልግሎቶችን በመስጠት ተደራሽነቱን እያሰፋ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

የዲጂታል ባንክ አገልግሎት አማራጮችን ለማስፋት በተሰራው ስራም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ የሞባይል ባንክ አገልግሎት ደንበኞች ቁጥር 3,377,554 የደረሰ ሲሆን የኢንተርኔት ባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ደግሞ 22,347 መድረሱን እንዲሁም የባንኩ የተቀማጭ ሂሳብ ደንበኞች ቁጥር 4,376,461 የደረሰ ሲሆን በመላው ሃገሪቱ የከፈታቸው ቅርንጫፎች ቁጥርም 455 መድረሱን ሰብሳቢው አመልክተዋል።

የባንኩንና የባንኩ ተቀጽላ የሆነው የወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ የተጣመረ እንዲሁም የትርፍ ድርሻን በተመለከተ ደግሞ የባንኩ የተናጠል የሂሳብ ሪፖርት መሰረት ባደረገ በቀረበው የባንኩ የኦፕሬሽን እና የፋይናንስ አፈፃፀም በተመለከተ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ ብር 66.5 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ27.5 በመቶ እድገት ማሳየቱን፣ በተመሳሳይ የባንኩ ከወለድ ነጻ ተቀማጭ ገንዘብ ባለፈው በጀት ዓመት ከነበረው ብር 2.4 ቢሊዮን ጋር ሲነፃፀር የ94 በመቶ እድገት በማስመዝገብ ብር4.78 ቢሊዮን መድረሱን፣ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎቶችን ለደንበኞች የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ በበጀት አመቱ ተጨማሪ ቅርንጫፎች እንዲከፈቱ መደረጉን፣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ባንኩ ያገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን 273 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲሆን ይህም ባለፈው የበጀት ዓመት ከተገኘው 305 ሚሊዮን ዶላር አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀር የ11 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱን ሰብሳቢው ገልጸዋል።

የንግድ ማህበረሰቡን የፋይናንስ ፍላጎት ከማሟላት አንጻር ባንኩ በበጀት ዓመቱ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ብድር ያቀረበ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የባንኩ አጠቃላይ ብድር መጠን ከባለፈው በጀት ዓመት አጠቃላይ የብድር መጠን ጋር ሲነፃፀር የ18 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 53.5 ቢሊዮን መድረሱን፤ የተሰጡ ብድሮችን በወቅቱ ከማስከፈል አንፃርም በሪፖርት ዘመኑ ብር 18.4 ቢሊዮን ብድር መሰብሰብ መቻሉ ተገልጸጻል።

እንዲሁም የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ካለፈው ዓመት የ28.8 በመቶ ጭማሪ በማሳየት ብር84.7 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን የባንኩ አጠቃላይ ካፒታል ብር 12.8 ቢልዮን መድረሱን፣ የተከፈለ ካፒታሉ ደግሞ የብር 1.9 ቢሊዮን ወይም 38.9 በመቶ እድገት በማሳየት በዓመቱ መጨረሻ ላይ ብር 7.02 ቢሊዮን ሲደርስ የቻለ መሆኑንና ለዚህ እድገት ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ባለአክሲዮኖቻችን ላለፉት ዓመታት የተደለደለላቸውን የትርፍ ድርሻ በአብዛኛው ለካፒታል ማሳደጊያ እንዲውል በመፍቀዳቸው እና አዳዲስ ተጨማሪ አክሲዮኖች በመግዛት በከፍተኛ ደረጃ በመሳተፋቸው በመሆኑ ቦርዱ ሳቅ ያለ ምስጋናውን እንደሚያቀርብ ለብሳቢው ገልጸው፣ ቦርዱና ማኔጅመንቱም ባለአክስዮኖች በባንኩ ሊሚያፈሱት ኢንቨስትመንት ተገቢውን ትርፍ እንዲያገኙ በመንቀሳቀስ ባለአክዮኖችን የሚያስደስት አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ አስገንዝበዋል።

ገቢን በተመለከተ ለብሳቢው በበጀት ዓመቱ ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች ባንኩ ብር 13.5 ቢሊዮን አጠቃላይ ገቢ ማስመዝገብ መቻሉንና ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ብር 9.8 ቢሊዮን ክንውን ጋር ሲነጻጸር የ38 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን፣

በሌላ በኩል በበጀት አመቱ የባንኩ አጠቃላይ ወጪ ካለፈው በጀት ዓመት አንጻር የ27 በመቶ ወይም የብር 2.1 ቢሊዮን ጭማሪ በማሳየት ወደ ብር 9.6 ቢሊዮን ከፍ ማለቱንና ከባንኩ ወጪ ከፍተኛውን የ41 በመቶ ድርሻ የሚይዘው የሰራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ሲሆን የወለድ ወጪ 33 በመቶ እንዲሁም አጠቃላይ ወጪ 20 በመቶ ድርሻ የያዙ መሆኑን፣ በበጀት ዓመቱ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እና በባንኩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በድምሩ 1,560,000 እንዲሁም ከትርፍ ላይ የሚከፈል አመታዊ የአገልገሎት ክፍያ በድምሩ 1,500,000 ብር መጠባበቂያ የተያዘ ሲሆን ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የተሰጠ ብድር ያለመኖሩን፣ በሌላ በኩል ለባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ በአመቱ የተከፈለ ደመወዝ መጠን ብር 7,981,780 ሲሆን ብር 14,485,555.48 ደግሞ ለጥቅማጥቅም በመክፈል በድምሩ ብር 22,467,335.48 ደመወዝና ጥቅማጥቅም መክፈሉን አስረድተዋል።

በዚሁም መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ባንኩ ከታክስ በፊት ብር 3.85 ቢሊዮን ትርፍ ያስመዘገበ ሲሆን ይህም ክንውን ካለፈው በጀት አመት ከተመዘገበው የብር 2.2 ቢልዮን ትርፍ በላይ የሆነ እንደሆነ፣ ከታክስ በኋላ የተገኘው ትርፍም ብር 2.78 ቢሊዮን እንደሆነና በዚህም መሰረት እያንዳንዱ አክሲዮን ያስገኘው ትርፍ (Earning Per Share) 46.10 በመቶ እንደሆነ ይህም ባለፈው አመት ከተገኘው 36.89 በመቶ ጋር ሲነጻጸር በአንድ አክሲዮን ከፍተኛ ብልጫ እንዳለው በመግለጽ፣ ከታክስ በኋላ ከተገኘው ትርፍ ህጋዊ መጠባበቂያ (Legal Reserve) እና የተቆጣጣሪ

አካል ስጋት ተጨማሪ መጠባበቂያ (Regulatory Risk Reserve) እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀደም ሲል እ.ኤ.አ 2022/23 በጀት ዓመት በስተቀር ከ2018/19 እስከ 2023/24 ድረስ በተቆጣጣሪ አካል ስጋት በተጨማሪ መያዝ የነበረበት መጠባበቂያ በአጠቃላይ ብር 118.14 ሚሲዮን ለባለአክሲዮኖች ትርፍ ክፍፍል የዋለ በመሆኑ ከዚህ ዓመት ለክፍፍል ከሚቀርበው ትርፍ እንዲቀነስ የተወሰነ ስለሆነ ይኸው መጠን ተቀንሶ ቀሪው ብር 1,948,123,862.92 ለትርፍ ድርሻ ክፍፍል እንዲውል ለባለአክስዮኖች ውሳኔ መቅረቡን አስታውቀዋል፡፡

በመቀጠልም ሰብሳቢው በቀጣይ በጀት አመት ባንኩ በኢንዱስትሪው እየመጡ ካሉ ለውጦች ተጠቃሚ የሚሆንበትን እድል በማስፋት ተወዳዳሪነቱንና ትርፋማነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን ፤ በዚህም የባንኩን የሃብት ማሰባሰብ አቅም ለማሳደግ የተደረጉ መዋቅራዊ ማስተካከያዎችን በመተግበር ስዲስትሪክት ጽ/ቤቶች እና ቅርንጫፎች ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ ሰፊ መሰረት ያለው ተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ፤ ከገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት እና የውጪ ምንዛሪ ምንጭ ካላቸው ድርጅቶች ጋር ያለን መልካም ግንኙነት በማጠናከር የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፤ እንዲሁም ተበዳሪ ደንበኞች ብድራቸውን በሰግባቡ እና በወቅቱ እንዲከፍሉ በመከታተል ከፍተኛ ሃብት ለማሰባበሰብ ጥረት የሚደረግ ሲሆን የተገኘው ሀብትም ውጤታማ በሆነ መስክ ላይ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች፤ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች ይበልጥ ደግሞ ከባንክ ስርዓት ተጠቃሚነት ርቀው ለቆዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለወጣትና ሴት ስራ ፈጣሪዎች ፋይናንስ በማቅረብ ሁለንታናዊ ለውጥ ለማምጣት እንደሚሰራ አስረድተዋል፡፡

ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል መጠን ከሚጠበቀው የጊዜ ገደብ አስቀድሞ ያሳካ ቢሆንም 2015 ዓ.ም በተደረገው 14ኛ አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን ካፒታል በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2020 ዓ.ም ወደ ብር 20 ቢሲዮን ለማሳደግ በተወሰነው መሰረት እና በኢንዱስትሪው እየተስተዋሉ ያሉ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት በተለይም ባንኩ በዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅ ለማስቻል የተከፈለ ካፒታሉን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ ባለአክሲዮኖች በባንኩ ባላቸው ኢንቨስትመንት ውጤታማነት ላይ አለአቸሁን ያሳዩትን እምነት በማስቀጠል በተያዝው በጀት ዓመትም የሚደለደልላቸውን የትርፍ ድርሻ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ እንዲያውሉት ቦርዱ ጥሪውን በአክብሮት እንደሚያቀርብ አስታውቀው፤ ሰቀም እና ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት አክሲዮን እንዲገዙ ለማበረታታት ይከፈል የነበረውን የ20 በመቶ አገልግሎት ክፍያ በማስቀረት አዳዲስ ኢንቨስተሮችን በመሳብ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ጥረት እንደሚደረግ አመልክተዋል፡፡

በተያያዘም የፋይናንስ ሴክተሩን ለውጪ ባንኮች ክፍት ማድረጉን ተከትሎ በኢንዱስትሪው በሚጠበቀው የመዋቅር ለውጥ በአገር በቀል ባንኮች መካከል እንደየሁኔታው በፈቃደኝነት ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ የሚፈፀም ውህደት እንዲሁም የውጪ ባንኮችን በባለአክሲዮንነት በማሳተፍ የሚፈጠር አጋርነት ሊፈፀሙ የሚችሉ አማራጮች ሲሆኑ ወጋገን ባንክ ስሙን እና ተወዳዳሪነቱን ጠብቆ ለመቀጠል የሚችልባቸው የተሻሉ አማራጮች ላይ እየተሰራ እንደሚገኝና በዚህ ሂደት ባለአክሲዮኖች የባንኩን የተከፈለ ካፒታል ይበልጥ ለማሳደግ የሚያደርጉት ሙሉ ድጋፍ እጅግ ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በተጨማሪም ፈጣን ለውጥ ላይ ባለ የባንክ ዘርፍ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ሆኖ ለመዝለቅ የባንኩን የቴክኖሎጂ ስርዓት ለማዘመን ከፍተኛ በጀት ተመድቦ በስፋት ሲሰራ የቆየ መሆኑንና በዚህም ለባንኩ የወደፊት የዲጂታል እድገት ወሳኝ የሆነ መሰረት ለመጣል መቻሉን፤ በቀጣይም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በማድረግ ለደንበኞች ምቹ፣ ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ የዲጂታል ባንክ አገልግሎትን በማስፋፋት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ ሰብሳቢው ተናግረዋል፡፡

በተያያዘም በስራ ላይ ያለው የባንኩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ትግበራ ጊዜ በዚህ ዓመት የሚጠናቀቅ በመሆኑ የሚቀጥለው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ የባንኩን ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች በውል ባገናዘበ እና ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚዘጋጅ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸው፤ ቀጣዩ የእቅድ ጊዜ ብዙ ሁኔታዎች የሚለዋወጡበት እና የውድድር ሜዳውም እንደሚበረታ የሚጠበቅ በመሆኑ የባንኩ ቀጣይ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ሰፊ አለምአቀፍ የባንክ ልምድ ባለው የውጭ ሃገር አማካሪ እገዛ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ የውጭ አማካሪ ድርጅት መመረጡን፤ ይህም ውል የተያዘለት ተቋም የባንኩን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት ከማገዝ ባሻገር ስትራቴጂክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቦርዱን እና ዋና ስራ አስፈጻሚውን የሚያማክር እንደሆነ አስረድዋል፡፡

በዘርፉ ያለውን መዋቅራዊ ለውጥ እና ከፍተኛ ፉክክር ተቋቁሞ በተወዳዳሪነት ለመዝለቅ ባንኩ የሚያወጣውን እቅድ መሳካት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የሰው ኃይሉ በመሆኑ ውጤታማነትን የሚያበረታታ፣ የባለቤትነት ስሜትን የሚያዳብር፣ የበለጠ አቅምና ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች የሚስብና ይዞ ለማቆየት የሚያስችል ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር ዋና ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ እንደሚሆንና ሰራተኞችን ለነባራዊ እና ወደፊት ለሚከሰቱ ለውጦች ከወዲሁ ዝግጁ ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎችን በስፋት በመስጠት በተለይም የከፍተኛ አመራረን አቅም ለመገንባት ሰፊ ስራ የሚሰራ መሆኑን ሰብሳቢው አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም ምቹና ተስማሚ የባንክ አገልግሎቶችን በማቅረብ የገቢ ምንጮችን ማስፋት፣ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የተበላሹ ብድሮችን በመቀነስ የሃብት ጥራትን ማሻሻል፣ የስጋት አስተዳደርን እና ወጪ ቆጣቢ አሰራሮችን በማጠናከር የባንኩን ትርፋማነት እና ጠቅላላ ሃብት ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን ሰብሳቢው ገልጸው፣ በተያያዘም ባንኩ በመቐለ ከተማ የራሱን ህንፃ ለመገንባት የጀመረውን ስራ አጠናክሮ በመቀጠል የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ ተገቢ ክትትል እንደሚደረግ ሰብሳቢው አስረድተዋል፡፡

ሰብሳቢው አክለውም በተያዘው በጀት ዓመት የተወጠኑ እቅዶችን ለማሳካት እንዲረዳ ባንኩ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር፣ በካፒታል ገበያ የሚኖረውን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማሳደግ እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ከባንኩ እድገት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በመፍጠር የባንኩን መልካም ገፅታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በመጨረሻም ሰብሳቢው በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በራሳቸው ስም በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ለተመዘገበው አመርቂ ውጤት መገኘት አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት፣ በባንኩ ላይ እምነት በማሳደርና ከባንኩ ጎን በመቆም አብረው ሲሰሩ ለነበሩ ውድ ደንበኞች እና ባለአክሲዮኖች በሙሉ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሁም በትጋት በመስራት ባንኩን ለዚህ ውጤት ላበቁት የባንኩ የስራ አመራርና ሰራተኞች ልባዊ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በንግድ ህጉ አንቀጽ 348 እና 349 መሰረት የውጭ ኦዲተሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበው ሪፖርት የባንኩን አጠቃላይ ሁኔታ በትክክል የሚያሳይ መሆኑን በማረጋገጥ የባላአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት እንዲያጸድቀው ጠይቀዋል፡

ሰብሳቢው በመቀጠል ጉባኤተኛው በቀረበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ እንዲወያይበት የጋበዙ ሲሆን ከጉባኤው ተሳታፊዎች የሚከተሉት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

- ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና ሰራተኛ ተቀናጅተው በመስራት ባንኩ ከጥቂት አመታት በፊት አጋጥሞት ከነበረው ችግር በፍጥነት በመውጣት እጅግ አመርቂ ውጤት እንዲያስመዘግብ ስላደረገው ከፍተኛ ጥረትና ለተገኘው ውጤት ባለአክስዮኖች ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል፡፡ ባንኩ ካገኘው ጥሩ የፋይናንስ አፈጻጸም በተጨማሪ በእንዳስተሪው ቀዳሚ በመሆን በካፒታል ገበያ እና በሌሎች አዳዲስ ስራዎች ፈር ቀዳጅ ሆኖ እያደረገ ያለው ንቁ ተሳትፎ የባንኩን መልካም ስም እና ደረጃ ከፍ ያደረገ በመሆኑ የሚያኮራ እንደሆነም ተገልጧል፡፡ በተጨማሪም በሀገሪቱ ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ለጊዜው የሚቻልበት በዲጅታል ላይ የተሰራውን አመርቂ ስራ በማጠናከርና እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፎችን በማስፋፋት፣ የጸጥታ ችግር ባለባቸው ትግራይ እና አማራ ክልሎች ጭምር ይበልጥ ተደራሽ ለመሆን እንዲሰራ፣

- ባንኩ አክስዮኖችን ለህዝብ እየሸጠ እንደሆነ፣ ተጨማሪ ካፒታል ለማሰባበሰብመ በአክስዮኖች ላይ የሚከፈለው አረቦን አስከማንሳት እንደሚሄድ ተገልጧል። ህጉ አክስዮኖች ለነባር ባለአክስዮኖች በቅድሚያ መቅረብ እንዳለባቸው ከሚያስቀምጠው አንጻርና ገና አዲስ እየተቋቋሙ ያሉ ድርጅቶች እንኳ የአገልግሎት ክፍያ እያስከፈሉ ባለበት ሁኔታ አሁን ላይ ባንኩ ትርፋማ እና ከፍተኛ ሃብት እያለው አዲስ ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ያለምንም የአገልግሎት ክፍያ በነጻ እንዲገዙ የተደረገበት ምክንያት እንዲብራራ ተጠይቋል።
- በካፒታል ገበያ ባንኩ ቀድሞ መግባቱ እና ባንኩ ያቋቋመው "ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ አ.ማ." ለባንኩ ምን ጥቅም አስገኝተዋል፣ ካፒታል ገበያ ላይ ቀድሞ መመዝገቡ እና የኢንቨስትመንት ባንክ ማቋቋሙ ላይ ባንኩ የወሰነው ጉዳት እና ጥቅሙ እንዲሁም አዋጪነቱ ከሌሎች የሰለጠኑና ከአፍሪካ ገረቤት ሀገራት ልምድ በመማር በሰገባቡ ተጠንቶ እና ተገምግሞ የተገባበት ስለመሆኑ ቢገለጽ በተለይ ኢንቨስትመንት ባንኩ ከስሯል የሚል ሪፖርት ስላለ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ባንኩ ከውጭ ትላልቅ ባንኮችን ተቋማት ጋር አብሮ በመስራት ተገኝ የተባለው ድጋፍ ምን አይነት ነው፣ ባንኩ በካፒታል ገበያ እና በሰነድ መዋእለ ነዋዮች ገበያ ከተመዘገበ በኃላ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? የባንኩን የሼር ዋጋስ ተተምኗል?
- ባንኩ ከነበረበት ሁኔታ አንጻር የተመዘገበው ውጤት አበረታች ቢሆንም ከሌሎች አቻ ባንኮች አፈጻጸም እና ባንኩ መድረስ ከነበረበት ደረጃ አንጻር አነስተኛ በመሆኑ በተገኘው ውጤት ረክቶ መዘናናት ሳያስፈልግ ይበልጥ ተነሳስቶ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ተጠናክሮ መስራት እንደሚገባና የተገኘውን አበረታች ውጤት አጠናክሮ በማስቀጠል በእንዱስትሪው እየመጡ ካሉ ፈታኝ ሁኔታዎች አንጻር ባንኩ በዘላቂነት ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ እድገቱም ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያስችሉ ስራዎች በትኩረት መስራት እንዲቻል ባለአክስዮኖች አስገንዝበዋል።
- አሁን ላይ የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠል ባለአክሲዮኖችም የበኩላቸው አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው፣ ከዚህ አንጻር በሀብት ማሰባሰብ፣ ካፒታል ማሳደግ እና የተቀማጭ ሂሳብ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝት በማሳደግ እገዛ ማድረግ፤ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሚያደርጋቸው የባንክ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች ከባንኩ ጋር በመስራት እና የባንኩ አምባሳደር ሆኖ የባንኩን አገልግሎቶች በማስተዋወቅ እነ በስፋት በመጠቀም የባንኩን እድገት ለማገዝ የበኩልን ኃላፊነት መወጣት እንደሚያስፈልግ፤ ባለአክሲዮኖች ቤተሰቦቻቸውን በባንኩ ሂሳብ ከፍተው በባንኩ አገልግሎቶች እንዲጠቀሙ እና በባንኩ እንዲጠቀሙ በማደረግ ባንኩን ማገዝ እንደሚገባ በስፋት ተገልጧል።

- ከወጪ ቅነሳ አንጻር የባንኩ የስራ እንቅስቃሴ የሰው ሃይል እና የካፒታል አቅምንና ተጠቃሚነትን በአመጣጣኝ መሰራት አለበት እንደሚገባ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል ወሳኝ በመሆኑ ያለውን ከፍተኛ የሰው ሃይል ቁጥር በመቀነስና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የባንኩን አገልግሎት ለማሻሻል እና ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ መስራት ቢቻል፣
- የተደረገው እንቅስቃሴ እና የተገኘው ውጤት ከአምናው ጋር ሲነጻጸር ጥሩ ቢሆንም ለባንኩ አስተማማኝ እድገት ወሳኝ በሆኑት የቁጠባ ሂሳብ እድገት እና የውጭ ምንዛሬ ግኝት አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው። ሌሎች ባንኮች በቁጠባ ሂሳብና በውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ስራ ላይ ጥሩ እየሰሩ ባለበት ሁኔታ የባንኩ አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ቢገለጽ፣ በቀጣይ ጥሩ እንሰራለን የተባለው ምን ስትራቴጂ ተይዞ እንደሆነ እንዲብራራ ተጠይቋል።
- የባንክ እንዱስትሪው ለውጭ ባለሃብቶች ክፍት መደረጉ እና የውጭ ባንኮች እንዲገቡ መፈቀዱን ተከትሎ ሊኖር በሚችል ውህደት በኩል ምን እየተሰራ እንዳለ ቢብራራ፣ የሚሉ ጥያቄዎች፣ ገንቢ አስተያቶች እና ምስጋና በባለአክስዮኖች ቀርበዋል።

ከባለአክሲዮኖች በተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ ባጭሩ

በቀረበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎችና ለተሰጡ አስተያየቶች የዳይክተሮች ቦርድ ሰብሳቢውና የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በጋራ እንደሚከተለው ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

- ከባለአክስዮኖች ለተሰጠው ምስጋና መልሰው በማመስገን አብዛኛዎቹ ከተደራሽነት ማስፋት፣ ወጪን ማመጣጠንና የዲጂታል ስራዎችን ማስፋፋት ጋር በተያያዘ የተሰጡት አስተያየቶች ገንቢ በመሆናቸው ቦርዱ እና ማኔጅመንት ተቀብሏቸው በቀጣይ በእቅድ ውስጥ ተካተው የሚሰራባቸው እንደሚሆን፣
- ባንኩ የሚያደርጋቸው ኢንቨስትመንቶች ሁሉ አዋጭነታቸው እየተረጋገጠ እንደሚገባበት፣ ከካፒታል ገበያ ጋር በተያያዘ ከመጣው አዲስ ሁኔታ ባንኩ ተጠቃሚ ሲሆን የሚችልበት እድል ካለ ማወቅ እንዲቻልና ፕሮጀክቶችን ቀርፃ በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ቀደም ብሎ ቦርዱ እና የባንኩ ማኔጅመንት በተለያዩ የውጭ ሃገራት በቂ ስልጠናና ልምድ መቅሰሙን፣ በካፒታል ገበያ ቀድሞ በመግባት በሰነድ መዋዕለ ንዋዮች የመጀመሪያ ተመዝጋቢ በመሆን እና የመጀመሪያው የኢንቨስትመንት ባንክ በመመስረት ረገድ ባንኩ ከካፒታል ገበያ ለመሳተፍ እና በኢትዮጵያ ለነደመዋለ ንዋዮች ገበያ ለመመዝገብ ያለውን ጠንካራ አቅም ዝግጁነት ዳሰሳ በማስጠናትና የኢንቨስትመንት ባንክ የመመስረት አዋጭነት ሁለት አለማቀፍ አማካሪ ድርጅቶችን ቀጥሮ በማስጠናት ተከናውኖ እና አዋጪ መሆኑ ተረጋግጦ የተገባበት እንደሆነና በዚህም ባንኩ ፈርቀዳጅ ሲሆን መቻሉን፣ ይህም ቦርዱ በታሪኩ

የሚኮራበት ፍጻሜ እንደሆነና በመንግስት በኩልም ባንኩ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈበት ሲሆን የባንኩን መልካም ስም ለመገንባት እና በህዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንዲያድግ ያስቻለ ያስቻለ መኖኑን፣ ይህንም ተከትሎ በርካታ ድርጅቶች ከባንኩ ጋር ለመስራት ፍላጎት በማሳየት መስራት በመጀመራቸው የባንኩን የሃብት ማሰባሰብ ጥረት ሊያግዝ መቻሉ፣ በተጨማሪም ኢንተርናሽናል ፋይናንስ ኮርፖሬሽን (አይ-ኤፍ-ሲ)፣ኮመርዝ ባንክ፣ እና ሲቲ ባንክ ከመሳሰሉ የተለያዩ አጋር ድርጅቶች እና የታወቁ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር አጋርነት በመመስረት ልምድ መቅሰም እና የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት መቻሉ ተብራርቷል፡፡

'ወጋገን ካፒታል ኢንቨስትመንት ባንክ' ተቋቁሞ ስራ የጀመረው ከግማሽ አመት በኃላ በመሆኑ ስራ ለመጀመር ለዝግጅት የወጡ የሰው ኃይል እና ቁሳቁስ እንዲሁም የቢሮ ኪራይ ጨምሮ የወጡ የኢንቨስትመንት ወጪዎች ምክንያት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት መጠነኛ ኪሳራ ሊያስመዘግብ መገደዱን በመጥቀስ አሁን ላይ ኢንቨስትመንት ባንኩ ቀድሞ ስራ በመጀመሩ ምክንያት በካፒታል ገበያ ለመመዝገብ የተዘጋጁ ብዙ ተቋማት ጋር የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ስምምነቶች መፈጸሙንና ወጤቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ይስተካከላል ተብሎ እንደሚታመን ተገልጧል፡፡

- ባንኩ በህጉ መሰረት ቅድሚያ ለነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮኖችን በመደልደል ተጨማሪ አክሲዮኖችን እንዲገዙ ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ነባር ባለአክሲዮኖች የተደለደለላቸውን አክሲዮኖች በተሰጠው የጊዜ ገደብ በሚፈለገው መጠን አክሲዮኖችን ሊገዙ ባለመቻላቸው በተደጋጋሚ ማሳሰቢ በመስጠት የቀሩ ያልተሸጡ አክሲዮኖችን ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለአዲስ ባለአክሲዮኖች ሽያጭ እየተከናወኑ መሆኑ ተገልጻል፡፡
- ባንኩ ከጥቂት አመታት በፊት አጋጥሞት ከነበረው የስም መጥፋት ዘመቻ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል የባንኩን አክሲዮኖች በመሸጥ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ያልተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሮ የነበረ በመሆኑ እንደአማራጭ ቀደም ሲል ሲያስከፍል የነበረውን ፕሪሚየም /premium/ ክፍያ እና መግዛት የሚቻለውን ዝቅተኛ የአክሲዮን መጠን በመቀነስና በአነስተኛ ፕሪሚየም አክሲዮኖችን ለመሸጥ ጥረት ሲደረግ የቆየ ሲሆን አሁን ላይ የባንኩ ስም መሻሻሉንና ትርፋማነቱም አዮደገ መምጣቱን ተከትሎ አነሰስተኛው አክስዮን ግዥ መጠንን የሚከፈለው አረቦን ተስቲካክሎ ባንኩ አክስዮኖችን በመሸጥ ላይ ቆይቷል፡፡ አክስዮኖች ለህዝብ የቀረቡት ቅድሚያ ለባለአክስዮኖች ተደልድለው ሳይፈረሙ የቀሩትን እንደሆነ፣ ባለአክስዮኖች አሁንም ቢሆን ሙሉ በሙሉ አክስዮኖቹን ራሳቸው ቢያስቀሩዋቸው ቦርዱና ማነጅመንቱ ደስተኞች እንደሆኑ፣ ይህ ሲሆን ባለመቻሉ ግን የባንኩን የካፒታል አቅም ማሳደግ ያለውን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለየ ሁኔታ ከ50 ሚሊዮን እና ከዛ በላይ በላይ የሆነ አክሲዮን በአንድ ጊዜ ሙሉ ክፍያ ለሚገዙ ትላልቅ

ተቋማትና ግለሰቦች ያስ ፕሪሚየም /premium/ እንዲገዙ መወሰኑን፤ ባለአክሲዮኖች የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ያሳዩት ፈላጎት ቦርዱ በደስታ የሚቀበለው መሆኑን በመግለጽም ባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻቸውን ለተጨማሪ አክሲዮን ግዥ ከማዋል በተጨማሪ አዲስ አክሲዮኖችን ግዥ እንዲፈጽሙ ቦርዱ ጋብዟል።

- የፋይናንስ ሴክተሩን ለውጪ ባንኮች ክፍት ማድረጉን ተከትሎ በኢንዱስትሪው የመዋቅር ለውጥ እንደሚኖር የሚጠበቅ በመሆኑ ባንክ ስሙን እና ተወዳዳሪነቱን ጠብቆ ለመቀጠል የሚችልባቸውን አማራጮች ከወዲሁ በመለየት የዝግጅት ስራ እየተሰራ ሲሆን ለእዚህም የሚስችል አቅም ከወዲሁ ለመፍጠር በሰው ኃይል አቅም ግንባታ፣ በቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ማሳደግ እና ዲጅታል የባንክ አገልግሎት ማስፋፋት እንዲሁም የባንኩን የተከፈለ ካፒታል በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ተብራርቷል ።
- አሁን ላይ የተገኘው ውጤት ከአምናው አንጻር የተሻለ ቢሆንም በዚህ መኩራራት ሳያስፈልግ ቦርዱ እና ማኔጅመንት ተቀናጅቶ የተሻለ ስትራቴጅ ነድፎ በመንቀሳቀስ ለሚቀጥለው አመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚሰራ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ባንኩ አሁን ላይ ያለውን አቅም እና ተወዳዳሪነት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የባንኩን የአክሲዮን ዋጋ ለማስተመን የሚሰራ መሆኑም ተብራርቷል።

ለ. የተሰጡት ድምጾች ውጤት እና ጉባኤው ያሳለፈውን ውሳኔ

በቀረበው ዓመታዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ ከጉባኤተኞች ለተነሱ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ተቀባይነት አግኝተውና ገንቢ አስተያየቶች ታሳቢ ተደርገው ፣ ሪፖርቱን የሚቃወም ወይም ድምጸ-ተአቅቦ ካለ ተጠይቆ፤ 273 ድምጽ በያዘ አንድ ባለአክሲዮን ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ሪፖርቱ ፀድቋል።

6.5. አጀንዳ 5.5፣ እ.ኤ.አ የ2024/2025 የሥራ ዘመን የውጭ ኦዲተር ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፦

ሀ. የውይይት አጭር ማጠቃለያ

የባንኩን እ.ኤ.አ የ2024/25 የሥራ ዘመን የባንኩን ሂሳብ እንዲመረምር ከተፈቀደው ድርጅት መደብኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ታፈሰ፣ ሽሰማ እና አያሌው የተመሰከረላቸው ኦዲት ስራ አስኪያጅና ማህበር የተባለ የውጭ ኦዲተር መመረጡን የጉባኤው ሰብሳቢ አስታውሰው፣ ማኅበሩ የባንኩን እ.ኤ.አ የ2024/25 የሂሳብ መግለጫዎች የመረመረ መሆኑን በመግለጽ የኦዲትና ማጎበሪ ተወካይ ይህንኑ የሂሳብ ምርመራ መግለጫ እንዲያቀርቡ ጋብዘዋል።

የውጭ ኦዲተሩ ድርጅት ተወካይ አቶ ሚክያስ ጸጋዬ ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የኦዲት ስራቻውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት እ.አ.አ ጁን 30 ቀን 2025 ስተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የተዘጋጁትን የባንኩ በአጠቃላይ እና በተናጠል የሀብትና ዕዳ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ እና ሌሎች ጠቅላላ ገቢዎች መግለጫ፤ በተጣራ ሃብት ላይ የታየ ለውጥ መግለጫ ፤ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ እንዲሁም ኩባንያው የሚከተላቸውን በአጠቃላይ እና በተናጠል የሂሳብ አሰራር ፖሊሲዎች እና ማብራሪያዎች ያካተቱትን የሂሳብ መግለጫዎች መመርመራቸውን ገልፀዋል፡፡ የኦዲት ስራቸውን ያከናወኑት በአለምአቀፍ የኦዲት ስራ ደረጃዎች (ISA) እና የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች የስነምግባር ደረጃዎች ቦርድ ለሂሳብ ባለሙያዎች ያወጣው የስነ-ምግባር ኮድ በሚጠይቀው እና በኢትዮጵያ ውስጥ ስተካሄደው ኦዲት አስፈላጊ በሆኑት የስነምግባር መርሆዎች መሰረት ከአክሲዮን ማህበሩ ነጻና ገለልተኝነታቸውን በመጠበቅ ስነምግባራዊ ኃላፊነታችውን ባሟላ መልኩ መሆኑን ጠቅሰው፣ በእነሱ አስተያየት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች አለምአቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን (IFRS) ተከትለው የተዘጋጁ መሆኑንና በአጠቃላይ እና በተናጠል አክሲዮን ማህበሩ እ.አ.አ ጁን 30 ቀን 2025 የነበረውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም በዚያው ዕለት ላለቀው ዓመት የነበረውን የሂሳብ እንቅስቃሴ እና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት በሚገባ የሚያሳዩ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

በሌላ በኩል የውጭ ኦዲተሩ በአመቱ የሂሳብ መግለጫ ኦዲት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸውን ጉዳዮች ያቀረቡ ሲሆን የብድር መጠባበቂያ ወጪ/ኢምፕይርመንት ሎስ/ ውስብስብ የግምት ስራ በሚጠይቀው አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 9/IFRS 9/ መጠቀም እንዲሁም ባንኩ በሌሎች ተቋሞች ያለውን ኢንቨስትመንት ፌር ቫልዩ ግምት የተከናወነው ውስብስብ እና እንደ ዲስካውንት ሬት እና የወደፊት የጥሬ ገንዘብ ፍሰት የመሳሰሉት የተለያዩ የማይታዩ ግብአቶችን መጠቀም የሚጠይቅ የግመታ ሞዴል በመጠቀም በመሆኑ ግመታዎች እንደገማች ለውጥ ያለያይ ስለሚችል በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ጉልህ ስህተት ሊያሳድር ይችላል የሚል ስጋት እንደሚኖር ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም ባንኩ በሌሎች ተቋሞች ያለው ኢንቨስትመንት ግምታ ምክንያታዊ እና አለምአቀፍ የሂሳብ ሪፖርት ደረጃ ቁጥር 13 የሚጠይቀውን ያሟላ ነው የሚል እምነት ቢኖራቸውም ባንኩ ከወደፊት ሊኖር የሚችለውን ጉልህ ስህተት ለመቀነስ በአብዛኛው ሲታዩ የሚችሉ ግብአቶችን የሚያካትት የግመታ ዘዴ ባንኩ እንዲጠቀም እና በየጊዜው የኢንቨስትመንቶችን አረዳደም እየተከታተለ የግመታ ሞዴሉን እንዲያሻሽል ምክር ሰጥተዋል፡፡

8. በጉባኤው የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የማህበሩ ጸሐፊ ማረጋገጫ

እኛ የወጋገን ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና ጸሐፊ ከዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘው የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ በየስማችው የፈረማችው እና የከፈሏችው አክሲዮኖች ብዛት በስማችው አንፃር በተመለከቱት ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች ወይም ተወካዮቻቸው መስከረም 27 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 32ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘታቸውንና ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለፁትን ውሳኔዎች ማሳለፋቸውን በንግድ ሕግ አንቀጽ 387(1) መሰረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶች ላይ ስለተገለጽት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሳኔዎች ትክክለኛነት ስማችው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ስሚነሳ ማናቸውም የመብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ቄምር እናረጋግጣለን።

ተ.ቁ	የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ ስም ዝርዝር	ኃላፊነት	ፊርማ
1.	አቶ አብዲሹ ሁሴን	ሰብሳቢ	
2.	አቶ ወልደገብርሄል ናይዝጊ	ም/ሰብሳቢ	
3.	አቶ ፍቅሩ ጂሬኛ	አባል	
4.	አቶ ፍትህነገስት ገብሩ	አባል	
5.	ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (አቶ ገብረእግዚአብሔር ሓዱሽ)	አባል	
6.	ሱር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር (አቶ ዘንፉ አስፋው ገ/ትንሳኤ)	አባል	
7.	ኢዛና መአድን ልማት ኃላ/የተ/የግ/ ማህበር (አቶ ተስፋፅዮን ደስታ ተሰፋ)	አባል	
8.	አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/ የግል ማህበር (አቶ ሐሰን ዮሱፍ)	አባል	
9.	አቶ ሱራፌል በርሀ ወልዱ	አባል	
10.	አቶሓዱሽ ህንፃይ	የማህበሩ ጸሐፊ	

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/8 ጽ/ቤት አ/አ
ፈራሚው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል፡፡
ቁጥር ቅ8/ሰየ/002077/ሃከ/2018
15/4/2018

Documents Authentication & Registration Service Branch & Office